# “ከዚች ምድር እናጠፋችኋለን”

## በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የዘር ማፅዳት በኢትዮጵያ የምዕራብ ትግራይ ዞን

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የታተመ ISBN
978-1-62313-975-9
የሽፋን ንድፍ በራፋኤል ጂሜኔዝ
Index: AFR 25/5444/2022

አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚታገሉ ከ10 ሚሊዮን በላይ አባላት ያሉት ዓለምዓቀፋዊ እንቅስቃሴ ነው። ራዕያችን የሰው ልጆች ሁሉ፣ በዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ እና በሌሎች የዓለማቀፍ ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች የተቀመጡት መብቶች ተከብሮላቸው ማየት ነው።

ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ ርዕዮተአለም፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ሀይማኖት ነፃ ነን፤ የገንዘብ ምንጫችንም በዋናነት ከአባላቶቻችን እና ከህዝብ የምናገኘው ልገሳ ነው። በሁሉም ቦታ ከሰዎች ጋር በመተባበር እና በርህራሄ በመስራት ማህበረሰቦቻችንን ወደ ተሻለ ሁኔታ መለወጥ እንደሚቻል እናምናለን።

ለበለጠ መረጃ እባከዎን ድረ-ገጻችን ይጎብኙ፤ https://www.amnesty.org/en/

ሂሁማን ራይትስ ዎች በዓለም ዙሪያ የሰዎችን መብት ይጠብቃል። ጥቃቶችን በጥንቃቄ እንመረምራለን፤ እውነታውን በስፋት እናሳውቃለን፤ ባልስልጣኖች መብቶች እንዲያከብሩ እና ፍትህ እንዲያስከብሩም ጫና እናደርጋለን። ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ገለልትኛ የሆነ ዓለምአቀፋዊ ድርጅት ሲሆን፣ ሰብአዊ ክብርን ለማስከበር እና ለሁሉም የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ለማሻሻል የሚተጋው ንቁ እንቅስቃሴ አንድ አካል ሆኖ ይሰራል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች. ከ 40 በላይ ሀገራት ውስጥ ሰራተኞች ያሉት አለምአቀፍ ድርጅት ሲሆን፣ አምስተርዳም፣ ቤይሩት፣ በርሊን ፣ ብራስልስ፣ ቺካጎ፣ ጄኔቫ፣ ጎማ፣ ጆሃንስበርግ፣ ለንደን፣ ሎስ አንጀለስ፣ ሞስኮ፣ ናይሮቢ፣ ኒው ዮርክ፣ ፓሪስ፣ ሳን ፍራንሲስኮ፣ ሲድኒ፣ ቶኪዮ፣ ቶሮንቶ፣ ቱኒስ፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና ዙሪክ ውስጥ ቢሮዎች አሉት።

ለበለጠ መረጃ እባከዎን ድረ-ገጻችን ይጎብኙ፤ http://www.hrw.org

መጋቢት 2014

ISBN: 9781623139759

# “ከዚች ምድር እናጠፋችኋለን”

## በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የዘር ማፅዳት

## በኢትዮጵያ የምዕራብ ትግራይ ዞን

በ2013 ዓ.ም የጥቅምት ወር ማብቂያ ላይ በተካሄደ ወታደራዊ የማጥቃት ዘመቻ የመጀመሪያ ደረጃ ወቅቶች የተፈጸሙ ጥቃቶች ... 6

ከህዳር 2013 እስከ ሰኔ 2013 ድረስ በምዕራብ ትግራይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ... 7

ከሰኔ 2013 እስከ ታህሣሥ 2014 በምዕራብ ትግራይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ... 9

የቁልፍ ምክርሀሳቦች ማጠቃለያ ... 10

# ማጠቃለያ

ጎይቶም የ42 አመት  የትግራይ ተወላጅ አርሶ አደር ነው። በሰሜን ኢትዮጲያ፣ በምዕራብ ትግራይ በምትገኘውና በሰሊጥ፣ በማሽላ እና በጥጥ ምርቷ በምትታወቀው አዲ ጎሹ ነዋሪ ነበር። ጥር 9 ቀን፣ 2013 ዓ.ም. በሚኖርባት ከተማ የአማራ ልዩ ኃይል እና የአካባቢ ሚሊሻዎች የትግራይ ተወላጆችን ሲደበድቡ እና ሲያስሩ እቤቱ ሆኖ በአቀመ-ቢስነት ስሜት ተመልክቷል። የትግራይ ተወላጆች በአካባቢው ባለስልጣናት እና በአማራ የጸጥታ ኃይሎች ለወራት ማስፈራሪያ ሲደርስባቸው ቆይቷል። በመሆኑም  ጎይቶም ከመጨረሻው ጥቃት ለማምለጥ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ጫካ ገብቶ ሁኔታው እስኪበርድ ድረስ ተሸሸገ። ከአንድ ቀን ቆይታ በኋላ አዲ ጎሹ ላሉ ዘመዶቹ ሲደውል፣ የጸጥታ ኃይሎቹ በደርዘን የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን ሰብስበው በተከዜ ድልድይ ላይ በጅምላ እንደፈጇቸው ተነገረው። ስለ ሁኔታው እንዲህ ሲል ተናሯል፤

> *ቁጥራችን ቀን በቀን እየቀነሰ ነበር። ከተከዜ ክስተት በኋላ የትግራይ ተወላጆች በብዛት ወጡ። እዛ የምንኖርበት ምንም ምክንያት አልነበረም። እኛ የከተማው አካል አልነበርንም። ከተማዋ በሌሎች ሰዎች ተወስዳለች። እንድንኖር አልተፈቀደልንም።*

*እዛው ቢቀር ለህይዎቱ ስለሚያሰጋው በሺዎች በሚቆጠሩት እንደ ሌሎች የትግራይ ተወላጆች ሁሉ አካባቢውን ጥሎ እንዲሸሽ ተገደደ፤ ሌሎች ደግሞ እንደዋዛ ከግዛቱ ተባረሩ። ከአማራ ባለስልጣናት እና ከክልል የጸጥታ ሃይሎች ለማምለጥ የተከዜን ወንዝ ወደ ምስራቅ ተሻግረው ወደ ሰሜን ምዕራብ ትግራይ አቀኑ።  የተቀረው ዓለም እይታውን ነፍጓቸው፣  በምዕራብ ትግራይ ዞን የሚደርስባቸውን ጥቃት ለማምለጥ በገፍ ከሸሹት የትግራይ ተወላጆች መካከል ጎይቶም አንዱ ነበር፤ ግጭቱም በቀጠለበትና ዓለምም ፊቱን ባዞረበት ተከታታይ የጅምላ ስደቶች ደግመው ደጋግመው ተከሰቱ።*

ጦርነቱ ከተቀሰቀሰበት ጥቅምት 25 2013 አንስቶ (ከኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስትን የወገኑ ኃይሎች፣ በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የሚመራውን  የትግራይ ክልል መንግስትና በሚፋለሙበት ወቅት) በምዕራብ ትግራይ የሚኖሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች፣ ማስፈራራት እና በኃይል የማስወገድ ዘመቻ ተካሂዶባቸው ከመኖሪያ ቤታቸው  ተገደው እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል።

በመላ አካባቢው በሚገኙ ማህበረሰቦች ላይ ለሚደርሱ ህግን ያልተከተሉ ግድያዎች፣ አስገድዶ መድፈሮች እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃቶች ተጠያቂዎቹ  በአዲስ በተሾሙ የአማራ እና የወልቃይት ባለስልጣናት የሚመሩት የአማራ የጸጥታ ኃይሎች ናቸው። መጠነ-ሰፊ የሰብልና የከብት ዘረፋ፣ የትግራይ ተወላጆች ቤት ቅሚያና ወረራ፣ የህዝቡን የኑሮ ምንጭ አውድሟል። የትግራይ ተወላጆች፣ በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ እስር ቤቶች ለጅምላ እና ረዘም ላለ የዘፈቀደ እስራት ተዳርገዋል፤ በእነዚህ እስር ቤቶችም አንዳንዶቹ ተገድለዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተጎሳቁለዋል። የክልሉ ባለስልጣናት የትግራይ ተወላጆችን መሰረታዊ አገልግሎቶችን እና ሰብአዊ እርዳታን የሚነፍጉ አድሎአዊ ህጎችን ደንግገዋል፤ የትግራይ ተወላጆች ከአካባቢው  እንዳይይቆዩ የሚያደርጉ እና እነርሱን ለማፈን የተዘጋጁ የሚመስሉ እርምጃዎችን አውጥተዋል። በትግሪያዊ

ማንናታቸው ላይ ያነጣጠረ  ብሄርን መሰረት ያደረጉ ስድቦችን ተሰድበዋል፤ ባፍ መፍቻ ቋንቋቸው፣ በትግርኛ እንዳይናገሩ ተከልክለዋል። አካል ጉዳተኞች እና አዛውንቶችም እንዲሁ ሰለባ ሆነዋል።

ይህ ሪፖርት፣ በአምነስቲ ኢንተርናሽናል እና በሂዩማን ራይትስ ዎች በታህሳስ ወር የተደረጉ 427 ቃለመጠይቆች እና በህዳር 2013 እና በመጋቢት 2014 መካከል የተደረጉ  ሌሎች ጥናቶችን መሰረት ያደረገ ነው፤ ከዚህ ሌላ፤  ቀደሞ ለጥናቱ ዳራ እና ዐውድ ያገለገሉ ሌሎች ጥናቶችንም እንደ ግባት ተጠቅሟል። በሁለቱ ተቋማት የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው፣ ከህዳር 2013 ጀምሮ፣ የምዕራብ ትግራይ የሲቪል ባለስልጣናት እና የአማራ ክልል የጸጥታ ሃይሎች (በኢትዮጵያ ፌዴራል ሃይሎች ስምምነትና  ምናልባትም ተሳትፎ) በርካት ከፍተኛ በደል ፈጽመዋል፤ ይህም፣ የትግራይ ተወላጅ በሆኑ ሰዎች ላይ የሚደረግ መጠነ-ስፊ እና ስልታዊ ጥቃት አካል ሲሆን፣ በሰው ልጆች ላይ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የጦር ወንጀሎች ጋር የሚተካከል ነው። እነዚህ ወንጀሎች፣ ግድያን፣ አስገድዶ መሰወርን፣ ማሰቃየትን፣ ማፈናቀልን ወይም አስገድዶ ማዛወርን፣ አስገድዶ መድፈርን፣ ወሲባዊ ባርነት እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃቶችን፣ ጭቆናን፣ ህገወጥ እስራትን፣ ምናልባትም ጨርሶ ዘር ማጥፋትን  እና ሌሎች ኢሰብአዊ ድርጊቶችን ያካትታሉ።

*የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እና የሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት፣ ምዕራብ ትግራይ ውስጥ በትግራይ ተወላጆች ላይ ለደረሰው የዘር ማጽዳት ወንጀል፣ የአማራ ክልል ባለስልጣናት እና የክልሉ ልዩ ሃይሎች እና ሚሊሻዎች (በፌደራል መንግስቱ ኃይሎች አባሪ-ተባባሪነት) ተጠያቂ መሆናቸውን ያሳያል። ምንም እንኳን መደበኛ የህግ ቃል ባይሆንም ወይንም  በአለም አቀፍ ህግ ውስጥ በውል የታወቀ ወንጀል ባይሆንም፣ “ዘር ማፅዳት”፣ የቀድሞዋን ዩጎዝላቪያ አስመልክቶ ለተባበሩት መንግስታት በቀረበ የባለሞያዎች ኮሚሽን የመጨረሻ ሪፖርት ላይ ፍች ተሰጥቶታል፤ በዚህ ፍች መሰረት፣ [“ዘር ማጽዳት”] በአንድ ብሄር ወይም ሀይማኖት ቡድን ለአላማ  የተዘጋጀ ፖሊሲ ሲሆን፣ ግቡም ኃይል እና ሁከትን በመጠቀም የሌላን ብሄር ወይም ሀይማኖት ቡድን አባል የሆኑ ሰላማዊ ሰዎችን ካንድ ከተወሰነ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ማስወገድ ነው። ይህ ዘገባ በግልፅ እንዳሳየው፣ በምዕራብ ትግራይ የተካሄደው የዘር ማፅዳት ዘመቻ የጦር ወንጀሎችን እና በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ጨምሮ ከባድ የሰብአዊ መብት እና የአለም አቀፍ የሰብአዊ ህግ ጥሰቶች በሚያመራ መልኩ የተከናወነ ነበር።*

ምዕራብ ትግራይ ውስጥ የነበሩ ውጥረቶች እና የመብት ረገጣዎች ለአመታት ሲብላሉ የቆዩ ናቸው፤ እነዚህ የመብት ረገጣዎች ሲደረጉ የነበሩት በዋናነት በትግራይ ክልል የጸጥታ ሀይላት ሲሆን የሚፈጸሙትም በአማሮች እና በወልቃይቶች(በታሪካቸው የትግርኛ እና አማርኛ ተናጋሪ ሆነው የኖሩ እና በምዕራብ ትግራይ ደጋ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች) ላይ ነው፤ ይህም፣ የኋላ ኋላ፣ በትግራይ ማህበረሰቦች ላይ በደረሰው አካላዊ ጥቃት እና ከአካባቢውም ለመባረራቸው እንደ ምክንያት ሆኖ አግልግሏል።  በምዕራብ ከሱዳን፣ በሰሜን ከኤርትራ፣ በደቡብ ደግሞ ከአጎራባች የአማራ ክልል የምትዋሰነዋ የምዕራብ ትግራይ ዞን በአማራ ክልል ባለስልጣናት ቁጥጥር ስር መዋል፣ በ1984 በህወሓት መራሹ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ፀድቆ የኢትዮጵያ የውስጥ ድንበሮች ውዝግብ  የቀየረ የሃይል ሚዛን  ለውጥ ያሳያል።

*በዛ ወቅት የኢትዮጵያ የውስጥ ወሰን በመንግስት የድንበር ኮሚሽን አመልካችነት እንደገና እንዲስተካከል የተደረገ ሲሆን ምዕራብ ትግራይን የሚያጠቃልሉት ቀደም ሲል በቀድሞው በጌምድር ክፍለ ሃገር የአስተዳደር ሥልጣን ስር የነበሩ ወረዳዎች ወደ ትግራይ ክልል ተካተዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ በምዕራብ ትግራይ ዞን እና በአማራ ክልል የሚኖሩ የአማራ አክቲቪስቶች የመንግስትን ውሳኔ ተቃውመዋል። በምላሹም፣ በግዛቱ ውስጥ የአማራነት ማንነታቸውን ለማስከበር የሚሞክሩትን እና*

የይገባኛል ጥያቄያቸውን ለክልሉ እና ለፌዴራል መንግስት የሚያቀርቡትን መንግስት በተለያየ ጊዜ በጭቆናና እና በኃይል አፍኖ ቆይቷል።

በጥቅምት 2013 የተቀሰቀሰው ግጭት እነዚህን የቆዩ እና ያልተመለሱ ቅሬታዎች ወደ ፊት ለፊት እንዲመጡ አድርጓቸዋል። ሆኖም፣ የአማራ ክልል ሃይሎች ከኢትዮጵያ ፌደራል ኃይሎች ጋር በመሆን እነዚህን ግዛቶች በመያዝ የትግራይ ተወላጆችን በአሰቃቂ የዘር ማጽዳት ዘመቻ አፈናቅለዋል።

## በ2013 ዓ.ም የጥቅምት ወር ማብቂያ ላይ በተካሄደ ወታደራዊ የማጥቃት ዘመቻ የመጀመሪያ ደረጃ ወቅቶች የተፈጸሙ ጥቃቶች

ጥቅምት 25 2013 ጦርነቱ ሲጀመር፣ ከባዱ ውጊያ መጀመሪያ ማዕከል ያደረገው በምዕራብ ትግራይ አስተዳደር ዞን የትግራይ ሀይሎች ላይ ነው። ጥቃቱን ያካሄዱትም ከኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሰራዊት እና ከአማራ ክልል የተውጣጡ ጥምር ሃይሎች (የአማራ ክልል ፖሊስ ልዩ ሃይል፣ የአማራ ሚሊሻዎች እና “ፋኖ በመባል የሚታወቁት ኢ-መደበኛ ሚሊሻዎች) ነበሩ። የኤርትራ አዋሳኝ የሆነችውን የሁመራ ከተማን ጨምሮ የፌደራል እና ጥምር ሃይሎች ከተሞችን እና መንደሮችን ደበደቡ። ጦርነቱ እየተደረገ ባለበት ወቅት፣ የትግራይ ኃይሎች ለመንግስት መረጃ ያቀብላሉ ብለው የጠረጠሯቸውን በጅምላ ረሽነዋቸዋል ቢባልም፣ በፍጥነት ከምዕራብ ትግራይ ተገፍተው እንዲወጡ ተደርገዋል።

በ10 ቀናት ውስጥ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ኃይሎች እና ጥምር ኃይሎቹ በመላው በዞኑ ውስጥ በሚገኙ የትግራይ ማህበርሰቦች ላይ ከጦር ወንጀሎች ጋር የሚተካከሉ አያሌ ጥቃቶችን ፈፅመዋል። እነዚህ ኃይሎች፣ መንደሮችን እና የሰፈራ ጣቢያዎቸን አውድመዋል፤ ንብረት፣ ከብቶች እና እህል ዘርፈዋል፤ የትግራይ ተወላጅ በሆኑ ሰላማዊ ሰዎች፣ በህወሓት ደጋፊዎች እና በአካባቢው የትግራይ ታጣቂዎች ላይ ከህግ አግባብ ውጭ የሆኑ ግድያዎችን፣ የዘፈቀደ እስራትንና ማሰቃየትን እና ሌሎች እንግልቶችን ፈጽመዋል። እነዚህ ጥቃቶች፣ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች በምዕራብ በኩል ወደ ጎረቤት ሱዳን፣ በምስራቅ ደግሞ ወደ ማዕከላዊ ትግራይ እንዲሰደዱ ምክንያት ሆነዋል።

በሱዳን ድንበር አቅራቢያ የምትገኘው የማይ ካድራ ከተማ የመጀሪያው በይፋ የተዘገበው መጠነ ሰፊ እልቂት የተፈጸመበት ቦታ ነበረች። ጥቅምት 30 ቀን (2013 ዓ.ም.) ከሰዐት ጀምሮ፣ የትግራይ ሚሊሻዎች እና የአካባቢው ነዋሪዎች በርካታ የአማራ ተወላጆችን በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድበዋቸዋል፤ በጩቤ ወግተዋቸዋል፤ በገጀራ እና በመጥረቢያ ቆራርጠዋቸዋል። በዚያው ምሽት ወደኋላ ላይ፣ የአማራ ተፋላሚዎች የበቀል እርምጃ በመውሰድ፣ የትግራይ ተወላጆችን ገድለዋል፤ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። በጥቃቱም በግምት 229 ሰዎች ሞተዋል። ተጨማሪ 100 ሰዎች፣ በዋነኛነት የአማራ ነዋሪዎች እና የጉልበት ሰራተኞች የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ወደ አካባቢው ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ተወስደዋል። የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት በጋራ ያደረጉት ጥናትም በተመሳሳይ መልኩ ከ200 በላይ ሰዎች መሞታቸውን አሳይቷል።

የፌደራል እና ጥምር ኃይሎቹ ማይ ካድራን ህዳር 1 ቀን 2013 ዓ.ም. ከተቆጣጠሩ በኋላ፣ የአማራ ልዩ ኃይል እና ሚሊሻዎች በቀጣዮቹ ቀናት የትግራይ ተወላጆች ላይ ተከታታይ የበቀል ግድያዎችን ፈጽመዋል።

ሸሽተው ያልሄዱት የትግራይ ተወላጆች በመደበኛ እና በጊዜያዊ እስር ቤቶች ታጉረዋል። የትግራይ ተወላጆች ንብረት ተዘርፏል፤ ተወርሷል። የጸጥታ ኃይሎች፣ የትግራይ ተወላጆች በዕስር ላይ እያሉ የእርዳታ አቅርቦት እንዳይደርሳቸው ከማደናቀፋቸውም በላይ፣ በስተመጨረሻ፣ በታህሳስ 2013 አጋማሽ አካባቢ፣ ከምዕራብ ትግራይ ተጭነው እንዲወጡ አድርገዋል።

ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ማይ ካድራ ውስጥ የተፈፀመው እልቂት በከተማው ውስጥ ከነበሩ የተለያዩ ሁኔታዎች ጋር የተቆራኘ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በከተማው ነዋሪዎች እና ከከተማ ውጭ በሚመጡ የጉልበት ሰራተኞች መካከል ቀደም ብሎ የነበረው ውጥረት፣ ከተማዋ በፍጥነት እየተጋጋለ ለመጣው በተፋላሚ ወገኖች መካከል ለነበረው ጦርነት ቅርብ መሆኗ እና በአካባቢው በፍጥነት ይሰራጭ የነበረው አሉባልታ ናቸው። በማይ ካድራው ጭፍጨፋ ወቅት ተፈጽመዋል ተብለው የተሰሙ የተለያዩ ወሬዎች፣ ከከተማዋ ባሻገርም ይበልጥ ጥላቻን፣ መፈራራትንና አለመተማመንን አባብሰዋል። ስለ ጭፍጨፋው የተሰሙ ወሬዎች ምእራብ ትግራይ በሚገኙ ሌሎች ቦታዎችም በትግራይ ተወላጆች ላይ የበቀል ጥቃት እንዲፋፋም አድርጓል።

በጭፍጨፋው ወቅት ስለተፈጸሙ ሁኔታዎች የሚሰሙ ወሬዎች፣ የፌደራል እና የአማራ ክልል ባለስልጣናት የሚያካሂዱት ጦርነት ተገቢ መሆኑን ለማስረገጥ እና ድጋፍን ለማሰባሰብ እንደ መሳሪያ አገልግለዋቸዋል። ማይ ካድራ ውስጥ የተፈጸመውን እልቂት ተክትሎ የተሰራጩ ወሬዎች፣ ምእራብ ትግራይ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ስፍራዎች በሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ላይም የበቀል ጥቃት እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆነዋል። ከጥቅምት 30 በኋላ ባሉት ቀናት፣ በከተማው ትግራይ ተወላጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ቀጥለዋል፤ ጥቃቶቹም፣ ተወላጆች ላይ ያነጣጣሩ ግድያዎችን፣ ዘረፋን፣ የጅምላ እስራት እና በተደራጀ መልኩ የትግራይ ተወላጆችን ከከተማዋ ማባረርን ያካትታሉ። ይህ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚደርሰው ጥቃት፣ በተከታዩ አመትም በግዛቱ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ቦታዎች በተመሳሳይ መልኩ እራሱን ደግሟል።

## ከህዳር 2013 እስከ ሰኔ 2013 ድረስ በምዕራብ ትግራይ የተፈጸሙ ጥቃቶች

*የፌደራልና የጥምር ሃይሎች ዞኑን ከተቆጣጠሩ በኋላም፣ ምዕራብ ትግራይ ለቀሩት በርካታ የትግራይ ተወላጅ ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆች ሰቆቃ አላበቃላቸውም። የአማራ ክልል ባለስልጣናት የአካባቢውን አስተዳደር ተረክበው እስከ አሁን በበላይነት እያስተዳደሩት ይገኛሉ። ጊዜያዊ ባለስልጣናቱም የተውጣጡት በምዕራብ ትግራይ ከሚገኙ የአካባቢው የወልቃይት፣ የአማራ ማህበረሰብ እና እንዲሁም ከአማራ ክልል ነው።*

*አዲስ የተሾሙት ባለስልጣናት፣ ዘር ላይ ያነጣጠሩ እቀባዎችን ደንግገዋል፤ እነዚህ ድንጋጌዎች ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ፤ የእርሻ መሬቶች የማግኘት መብት ላይ፤ እንዲሁም የትግራይ ተወላጆች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሆነው ትግርኛ አጠቃቀም ላይ ገደቦች ጥለዋል። የትግራይ ተወላጆች፣ በምዕራብ ትግራይ አዲስ የተሾሙ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ኃይሎች ሊያገኙ የሚገባቸውን መሰረታዊ የሆነ እርዳታ እንዳያገኙ እንዴት አድረገው ገደብ እንደሚጥሉባቸውና አንዳንዴም በቀጥታ እንደሚከለክሏቸው ገልጸዋል። የአማራ እና የፋኖ ሚሊሻዎች (አንዳንዴም የትግራይ ተወላጅ ካልሆኑ ነዋሪዎች እና ከኤርትራ ፌደራል ሃይሎች ጋር በመሆን) እህል እና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የቤት እንስሳትን ዘርፈዋል። እነዚህ በአመዛኙ በግብርና ስራ ለሚተዳደረው ማህበረሰብ፣ የኢኮኖሚ ህልውናና የገቢ ምንጭ የሆኑ የጀርባ አጥንቶች ናቸው። እነዚህ*

ንብረቶቻቸው ሲዘረፉባቸው፣ አካባቢውን ለቀው ከመውጣት በቀር በህይወት ለመቆየት ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። ባለስልጣናት እና የጸጥታ ኀይሎችም በሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን ማሰር ጀምረው ነበር።

ሁመራን፣ ሩዋሳን፣ አዲ ጎሹን፣ አዴባይ እና ባእከርን ጨምሮ፣ በበርካታ ከተሞች፣ የትግራይ ተወላጆችን ከአካባቢው የማስወገድ እቅድ ባደባባይ ውይይት የሚደረገበት እና የሚታይ ጉዳይ ነበር። የአካባቢው አስተዳዳሪዎች፣ እንደዚህ ያሉ እቅዶችን ከተማው ውስጥ በሚደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ወቅት በግልፅ የሚወያዩት ነገር ነበር። የትግራይ ተወላጆች እንዲወጡ የሚጠይቁ ማስታዎቂያዎች ተለጥፈው ታይተዋል። በ24 ሰዓት ወይም በ72 ሰአታት ውስጥ ለቀው የማይወጡ ከሆነ፣ እንሚገደሉ የሚገልጹ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያዎችን የያዙ በራሪ ወረቀቶችም ተሰራጭተዋል። ጊዜያዊ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ሃይሉ ሀላፊዎች፣ " የትግራይ ተወላጆች ቦታ ከተከዜ በስተ ምስራቅ ነው" እና "ይህ የአማራ መሬት ነው" የሚሉ መፈክሮችን እየደጋገሙ በማሰማት፣ የትግራይ ተወላጆች አካባቢውን ለቀው መውጣት እንዳለባቸው አስረግጠው ተናግረዋል።

ጥር 9 ቀን፣ 2013 ዓ.ም. ፋኖ በመባል የሚታወቀው የአማራ ሚሊሻዎች እና የአካባቢው ነዋሪዎች በደርዘን የሚቆጠሩ የአዲ ጎሹ ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ የትግራይ ተወላጆችን ሰብስበው አስረዋል።የአማራ ልዩ ኃይል አባላት ወደ 60 የሚጠጉ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ወንዶችን ተከዜ ወንዝ አጠገብ ሰብሰብው ገድለዋል። ኀይቶም [የተባለው የአካባቢው የትግራይ ተወላጅ] ያመለጠውም ከዚህ እልቂት ነው። ይህ ጭፍጨፋ፣ ቀደም ባለው ምሽት፣ የአማራ ኃይሎች ከትግራይ ኃይሎች ጋር ባደረጉት ውጊያ ለደረሰባቸው ከፍተኛ ኪሳራ የበቀል ጥቃት እንደሆነ እማኞች እና በህይወት የተረፉት ጥቂት ሰዎች ያምናሉ። በአዲ ጎሹ፣ ከጅምላ ጭፍጨፋው በኋላም፣ የጅምላ ፍልሰትን በሚያበረታታ መልኩ በትግራይ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለው ስደት ተባብሶ ቀጥሏል። በተከዜ ድልድይ የሸሹት የትግራይ ተወላጆች ለበርካታ ሳምንታት ያልተቀበሩትን አስከሬኖች ያዩ ነበር፤ ትዕይንቱም ለተፈፀመውን እልቂት ዘግናኝ አስታዎሽ ሆኖባቸዋል።

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እና የሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት በምዕራብ ትግራይ ያሉ ባለስልጣናት፣ የትግራይ ተወላጆች ለህልውናቸው ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን እንደነፈጓቸውና ወደ ሱዳን ወይም ወደ ሌላ የትግራይ ክፍል እንዲሰደዱ እንዳስገደዷቸው አሳይቷል። በአንዳንድ ቦታዎች፣ የአካባቢው ባለስልጣናት፣ የትግራይ ተወላጆችን ከአካባቢው በግድ ለማስወጣት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል። በዚህ ረገድ፣ የትግራይ ተወላጆችን ከመኖሪያ ቤታቸው ወይም ከታሰሩበት ቦታ ወደ ተከዜ ድልድይ ለመውሰድ የሚያገለግሉ የጭነት መኪናዎችን ወይም አውቶቡሶችን አዘጋጅተው አቅረበዋል፤ የተከዜ ድልድይ ደግሞ፣ ተፋናቃዮቹ አቋርጠውት የሚያልፉት እና በአዲስ መልክ በአማራ ባለስልጣናት ቁጥጥር ስር የዋለው አካባቢ የተካለለበት ወሰን ነው። ድልድዩ ላይ ዘብ የቆሙት የአማራ የጸጥታ ኃይሎች፣ የትግራይ ተወላጆች ድልድዩን እንዲሻገሩ ከመፍቀዳቸው በፊት፣ በዚህ የመጨረሻው የፍተሻ ኬላ፣ ተወላጆቹ የያዙትን መታወቂያ ወረቀቶች እና በምዕራብ ትግራይ ውስጥ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ዶክመንቶችን ነጥቀዋቸዋል፤ ወደ አካባቢውም ተመልሰው እንዳይመጡ አስጠንቅቀዋቸዋል። በሌሎች የትግራይ አካባቢዎች የተፈጠረውን ሁከት ሸሽተው የሚመጡ የትግራይ ተወላጆችንም ወደ ምዕራብ ትግራይ እንዳይገቡ ከልክለዋቸዋል።

በግዳጅ መፈናቀሉ በየካቲት እና መጋቢት 2013 አጋማሽ ድረስ ተባብሶ ቀጥሏል፤ በዚሁም የተነሳ፣ በተከዜ ወንዝ በስተምሥራቅ ወደሚገኙ ከተሞች፣ ማለትም እንደ ሽሬ፣ ሽራሮ እና በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ ትግራይ በምትገኘው አክሱም ባሉ ከተሞች የሚፈልሱ ተፈናቃዮች ቁጥር በእጅጉ ጨምሮ ነበር። በመሆኑም፣ በእነዚህ ከተሞች አያሌ ተፈናቃዮች፣ ለበርካታ ወራት በተፋፈጉ የመጠለያ ቦታዎች ውስጥ እንዲኖሩ ተገደዋል። በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም.፣ የትግራይ የፌዴራል ጊዜያዊ አስተዳደር ባደረገው የመጀመሪያ ዳሰሳ ጥናት፣ ከምዕራብ ትግራይ ተፈናቅለው ወደ ሌሎች የትግራይ አካባቢዎች የሰፈሩ ተፈናቃዮች ብዛት 723,000 እንሚደርስ አመላክቷል። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ (ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር) ደግሞ፣ በጥር ወር 2014 ዓ.ም፣. 51,207 ስደተኞች በምስራቅ ሱዳን ውስጥ እንደተመዘገቡ አስታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ጊዜያዊ ባለስልጣናት እና የአማራ ክልል ሹማምንት፣ የአማራ ተወላጆች ወደ ምዕራብ ትግራይ መጥተው እንዲሰፍሩ እና ቤትና መሬትም እንደሚሰጣቸው ቃል ገብተዋል።

# ከሰኔ 2013 እስከ ታህሣሥ 2014 በምዕራብ ትግራይ የተፈጸሙ ጥቃቶች

በሰኔ ወር አጋማሽ ላይ፣ የትግራይ ኃይሎች በርካታ የትግራይ አካባቢዎችን መልሰው መቆጣጠራቸውን ተከትሎ፣ የአማራ ባለስልጣናት እና ኃይሎች፣ በቀሪዎቹ የትግራይ ተወላጆች ላይ፣ በተለይም በሁመራ አዋሳኝ ከተማ እና በአቅራቢያው ባሉ ከተሞችና መንደሮች የሚደርሱትን የዘፈቀደ እስራት እና ግድያ አጧጡፈው ቀጥለውት ነበር። እስከ ነሃሴ ወር ድረስ፣ የትግራይ ተወላጆች እየተለቀሙና እየተገደሉ በነበረበት ሁኔታ፣ በደርዘኖች የሚቆጠሩ የመቆራረጥ ጉዳት የደረሰባቸው አስከሬኖች በተከዜ ወንዝ ውስጥ (በምዕራብ ትግራይ እና በሱዳን መካከል ያለውን ድንበር በሚያመለክተው) ታይተዋል። በህዳር ወር፣ በሁመራ፣ አዴባይ እና በራውያን ከተሞች፣ እስራቶችና መፈናቀሎች እንደገና ተባብሰው ቀጠሉ፤ ይህ የሆነው፣ የአማራ ልዩ ኃይል እና የፋኖ ሚሊሻዎች (አንዳንዴም ከኤርትራ ጦር ጋር በመተጋገዝ ) ወንዶችን በማሰር እና በርካታ ሴቶችን፣ ህፃናትን እና አዋቂዎችን ከመኖሪያ ቤታቸው ባስወገዱበት ወቅት ነው፣ ይህን የሚያደርጉት፣ ተፈናቃይዎቹን ወደ ተከዜ ወንዝ በግድ ከማባረራቸው በፊት ነበር። በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ጎልማሶች፣ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ለህይወት አስጊ በሆነ ስቃይ፣ ረሃብ እና የህክምና አገልግሎትን ተነፍገው በተጨናነቁ ቦታዎች በእስር ቤት እንዲቆዩ ተደርገዋል።

በግዳጅ መፈናቀሉና ሽሽቱ መጠን፣ ጥቃቶቹ የተፈፀሙባቸው መንገዶች እና በዞኑ ውስጥ ጥቃቶቹ የተፈፀሙባቸው ቦታዎች ብዛት፤ እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት ዞኑን በበላይነት እያስተዳደሩ ባሉ ባለስልጣናት፣ ማለትም በአማራ ክልል ኃይሎችና ሚሊሻዎች መካከል ምን ያህል የቁጥጥር፣ የቅንጅት እና አላማ እንድነት እንዳለ ነው፤ የዚህ ትብብር አላማ የሚመስለው የትግራይ ተወላጆችን አሽማቆ ከምእራብ ትግራይ ማስወገድ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን ከባድ የመብት ጥሰቶች ለማስቆም ወይም ተጠያቂዎችን ለመቅጣት ያደርገው ጥረት ፈጽሞ በቂ አልነበረም። በየካቲት ወር 2013 ዓ.ም. የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን፣ "በምዕራብ ትግራይ ብሄርን የማጽዳት ድርጊቶች ተፈጽሟል" በማለት ለሰጡት መግለጫ የሰጡትን ምላሽ ጨምሮ፣ የፌደራል እና የክልል ባለስልጣናት የዘር ማጽዳትን አስመልክቶ የሚቀርባባቸውን ክስ ውድቅ አድርገውታል። ከዚያን ጊዜ አንስቶ፣ የፌደራል ባለስልጣናት በማይ ካድራ የአማራ ተወላጆች እና ማህበረሰቦች ላይ የተፈፀመውን የጅምላ ግድያ አስመልክቶ የቀርቡ ሪፖርቶችን ፈትሸዋል፤ ይሁን እንጂ፣ በምዕራብ ትግራይ፣ በትግራይ ተወላጆች ላይ እየደረሱ ያሉትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በማጣራት ረገድ ምንም አይነት እርምጃ አልወሰዱም። እንዲያውም፣ መንግስት፣ ቤታቸውን ጥለው ወደ ሱዳን የተሰደዱ ስደተኞች የሚያቀርቡትን እሮሮ ማጣጣሉን ቀጥሎበታል። በምዕራብ ትግራይ የተፈጸሙ ግድያዎችና እስራት ተዓማኒነት ያላቸው ሪፖርቶች ቢሆኑም ቅሉ፣ መንግስት ግን ሁኔታዎችን "የሀሰት ወሬ " በማለት ያጣጥላቸዋል፤ በመሆኑም፣ የመንግስት መግላጫዎች፣ በህይወት ተርፈው ከአቅማቸው በላይ የመከራ ህይዎት እየተጋፈጡ ባሉ ተጎጂዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂውማን ራይትስ ዎች በዚህ ጥናት የቀረቡ ግኝቶችን በተመለከተ ምላሽ እንዲሰጡት የተለያዩ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት ባለስልጣናትን እና ኤጀንሲዎችን ቢያነጋግሩም፣ ምላሽ የሰጠው የአማራ ክልል መንግስት ብቻ ነው። በደብዳቤ የተላከው የክልሉ መንግሥት ምላሽም፣ የዚህ ጥናት ግኝቶችን የሚጻረር ምንም አይነት ተቃራኒ ማስረጃ አልቀረበበትም፤ ያንን በማድረግ ፋንታ፣ ጥናቱን "በህዝብ፣ በአስተዳደር እና በጸጥታ ሃይሎች" ላይ የተሰነዘረው ውንጀላ "መሰረተ ቢስ" እና "አሳሳቢ" በማለት አውግዞታል። እኛ የደረስንበትን ድምዳሜም፣ "መሰረተ ቢስ" ሲል ገልጾታል፤ "የትግራይ ተወላጆችን የማባረር ውንጀላንም" እንዲወጡ የተደረጉት ከአማራ ክልል እንጅ ከትግራይ ክልል አይደለም በማለትን ክሱን፣"ቅጥፈት" ነው ብሎታል።

በዚህ ዘገባ ላይ የተዘረዘሩት በደሎች፣ በምዕራብ ትግራይ የተፈፀመውን ሁሉ በተሟላ መልኩ ያካተቱ ባይሆኑም፣ ትርጉም ያለው ተጠያቂነትን እና እርምትን የሚሹ ናቸው። የኢትዮጲያ ባለስልጣናት፣ እነዚህን አካባቢዎች ለሰበዓዊ ኤጄንሲዎች ባልተደናቀፈ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የማሳለጥ ስራ መስራት አለባቸው፤ ይህንን መብት የሚሰጡት ገለልተኛ ለሆኑ የሰብዓዊ መብት ተቆጣጣሪዎች ሲሆን፣ ይህም በአፍሪካ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተቋቋመውን አጣሪ ኮሚሽን እና ኢትዮጵያን በተመለከተ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመውን አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽንን ያካትታል፤ የኢትዮጵያ ምዕራብ ትግራይን ጨምሮ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች ለእነዚህ አካላት ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል።

ለእነዚህ ጥቃቶች ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የተቀናጀ ዓለም አቀፍ ምላሽ ያስፈልገዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት እና የኢትዮጵያ አለም አቀፍ እና ክልላዊ አጋሮች በአደጋ ላይ ያሉ የትግራይ ተወላጆችን ጨምሮ ሁሉም ማህበረሰቦች በአፋጣኝ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ግፊት ለማድረግ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። በተጨማሪም፣ የተባበሩት መንግስታት ነፃ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በኢትዮጵያ ላይ የሚሰራውን ስራ ጊዜ ሳይስወዱ መደገፍ እና በሰሜን ኢትዮጵያ ከጥቅምት 2013 ጀምሮ በሁሉም ግጭቶች የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ረገጣ እና የጦር ወንጀሎችን ለማጣራት ወደ ስራ መገባቱን ማረጋገጥ አለባቸው። ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የትግራይ ተወላጆች ጥቃቱ እንደሚያበቃ እና ስቃያቸውንም አለም በስተመጨረሻ  እንደሚያውቀው ተስፋ አድርገዋል። መንግስታት ስቃያቸው በቸልታ የማይታይ መሆኑን ማረጋገጥ እና ተዓማኒነት ያለው ፍትህ እንዲገኝና እና ለተፈጸሙት ከባድ ወንጀሎች እርምት እንዲሰጥ ግፊት ማድረግ አለባቸው።

## የቁልፍ ምክርሀሳቦች ማጠቃለያ

### *ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት እና የክልል ባለስልጣኖች፤*

- በምዕራብ ትግራይ እና በሌሎችም አካባቢዎች በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊ ህግ ጥሰቶችን እንዲያቆሙ የፌዴራል እና የክልል የጸጥታ ኃይሎችን በይፋ እንዲያዙ።
- እንደ ፋኖ እና ሌሎች ሚሊሻዎች ያሉ መደበኛ ያልሆኑ ግፈኛ ኃይሎችን ከምዕራብ ትግራይ ባፋጣኝ እንዲያስወጡ እና ትጥቅ እንዲያስፈቱ።
- የአማራ ክልል ጊዜያዊ ባለስልጣናትን እና የጸጥታ ኃይሎችን ጨምሮ፣ ጊዚያዊ የሲቪል ባለስልጣናትን በምዕራብ ትግራይ ለደረሰው ከባድ ጥቃት እጃቸው ያለበት የጸጥታ ኃይሎች የተከሰሱበት ተግባር እስኪጣራ ድረስ ከአማራ ልዩ ኃይል እና ከኢትዮጵያ ፌደራል ኃይሎች እንዲያግዱ።
- በምዕራብ ትግራይ ዞን፣ ከ2013 ጥቅምት መጨረሻ  ጀምሮ በሰብአዊነት ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የጦር ወንጀሎች ተጠያቂ ሆነው የተገኙትን እንዳፈላጊነቱ እንዲቀጡ ወይም

ለፍርድ እንዲያቀርቡ። በዝህ ሪፖርት በስም በተጠቀሱ ሶስት ሰዎች ላይ ምርመራ እንዲያደርጉ።

- በተፋላሚ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ ሰላማዊ ሰዎችን ለመጠበቅ፣ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር እና ሰብዓዊ እርዳታዎችን ለማቅረብ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ጠንካራ ውክልና እና አቅም ያለውን በአፍሪካ ህብረት የሚመራ አለም አቀፍ የሰላም አስከባሪ ኃይል በምዕራብ ትግራይ ለማሰማራት እንዲፈቅዱ።
- በምዕራብ ትግራይ በዘፈቀደ የታሰሩትን ሁሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱ። የአማራ ጊዜያዊ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ኃይሎችም በምዕራብ ትግራይ ግጭቱ ከተጀመረበት ከጥቅምት ወር መጨረሻ 2013 አንስቶ ስለታሰሩት ሁሉም የትግራይ ተወላጆች እጣ ፈንታ በአስቸኳይ ለህዝብ መረጃ እንዲሰጡ። የኢትዮጵያ ባለስልጣናት አለም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ኤጀንሲዎች ያለቅድመ ማሳሳቢያ መደበኛ እና መደበኛ ወዳልሆኑ የእስር ቦታዎችን መግባት እንዲችሉና ታሳሪዎችም አፋጣኝ የምግብ፣ የውኃ እና የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲፈቅዱ።
- መሰረታዊ አገልግሎቶችን በአፋጣኝ ወደነበረበት በመመለስ ለሰብአዊ እርዳታ ኤጀንሲዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ቀጣይነት ያለው እና ያልተገደበ ተደራሽነትን በትግራይ ለሚገኙ የተጎዱ ህዝቦች ሁሉ እንዲያሳልጡ፤ በተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች እና ሰብአዊ ድርጅቶች ላይ ያስቀመጡትን የእርዳታ አቅርቦትን የሚያስተጓጉሉ ቢሮክራሲያዊና እና የመተላለፊያ ገደቦችን እንዲያስወግዱና ገለልተኛ የሆነ የእርዳታ ቁጥጥር እና ክትትልን እንዲፈቅዱ።
- ከተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ጋር በመመካከር እና የሚመለከታቸውን የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎችን በማሳተፍ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ እውቀትን መሰረት ያደረገና የሰዎችን ክብር በጠበቀ መልኩ ተመልሶ የመምጣትን ሂደትን የሚያቀናጅና የሚቆጣጣር ነጻ አካል ማቋቋም። የተፈናቀሉ ሰዎችን እና ስደተኞችን የመመለሱ ሂደት ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እና ለተመላሽ ህዝቦች ደህንነት እና ክብር ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን እንዲያረጋግጡ።
- የአስተዳደር ወሰኖችን ጨምሮ በቡድኖች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት የተቋቋመ ማንኛውም ስልት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ከገለልተኛ ተቋማት ጋር በመመካከር መስራቱንና የመመለስ መብትን ጨምሮ የግለሰቦችን ሰብአዊ መብቶች በተሟላ መልኩ የሚያከብር መሆኑን እንዲያረጋግጡ።

## *ለአፍሪካ ህብረት እና ለተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት፤*

- ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ዘላቂ እና ያልተገደበ ሰብአዊ እርዳታ እንዲደርስ ሁሉም የግጭቱ ተሳታፊ አካላት ላይ ጫና እንዲያደርጉ። የኢትዮጵያ መንግስት በትግራይ ባንክ፣ ኮሙዩኒኬሽን እና መብራትን ጨምሮ መሠረታዊ አገልግሎቶችን እንዲመልስ እንዲወተውቱ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌደራል እና የክልል ባለስልጣናትን በምዕራብ ትግራይ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ጥበቃ ተቆጣጣሪዎች በአፋጣኝ የመግባት ፍቃድ እንዲገኙ ግፊት እንዲያደርጉ።
- የፀጥታው ምክር ቤት አባል ሀገራት ኢትዮጵያን በምክር ቤቱ መደበኛ አጀንዳ ውስጥ በማስገባት በሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት ውስጥ በተሳተፉት አካላት ላይ ሁሉን አቀፍ የጦር መሳሪያ ማዕቀብ እንዲጥሉና የተባበሩት መንግስታት የክትትል አካልም ስለ አገዳው አፈፃፀም ሪፖርት እንዲየደርግ።
- በተፋላሚ ወገኖች መካከል እንደሚደረግ ማንኛውም የስምምነት አካል፣ የሲቪል ማህበረሰቡን ለመጠበቅ፣ ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር እና ሰባዊ እርዳታዎችን ለማቅረብ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ጠንካራ ውክልና እና አቅም ያለውን በአፍሪካ ህብረት የሚመራ አለም አቀፍ የሰላም አስከባሪ ሃይል በምዕራብ ትግራይ ለማሰማራት እንዲያግዙ።

- ከተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ጋር በመመካከር እና የሚመለከታቸውን የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎችን በማሳተፍ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ እውቀትን መሰረት ያደረገና የሰዎችን ክብር በጠበቀ መልኩ ተመልሶ የመምጣትን ሂደትን የሚያቀናጅና የሚቆጣጣር  ነጻ አካል እንዲቋቋም እንዲያግዙ።
- በዚህ ዘገባ ከተሰነዱት ወንጀሎች ግዝፈት አንፃር፣ በኢትዮጵያ ላይ የሚሰራው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ቡድን ኮሚሽን እንደምርመራው አካል፣ ከጥቅምት 2013 ጀምሮ በምዕራብ ትግራይ የነበሩ ሁኔታዎችን እንዲያካትት፤ በተቻለ መጠን ተጠያቂ የሆኑትን ግለሰቦች እንዲለይ፤ በአገር አቀፍ፣ በክልል እና በዓለም አቀፍ የፍትህ አካላት ጭምር አጥፊዎችን እንዴት ተጠያቂ ማድረግ እንደሚቻል ምክሮችን እንዲሰጡ።
- በአለምአቀፍ ስልጣን መርህ እና በብሄራዊ ህግጋት መሰረት በአለም አቀፍ ህግ በከባድ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ሰዎችን ምርመራ እና ክስን እንዲደግፉ።